ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

**የዩናይትድ ስቴትስ የመኖሪያ ቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት**
**የመኖሪያ ቤቶች ጉዳይ ቢሮ የባለ ብዙ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞች**

**የኪራይ መኖሪያ ቤቶች የይዞታ ማሻሻያ ፕሮጀክት**

## EIV እና እርስዎ

ኢንተርፕራይዝ የገቢ ማረጋገጫ

**በቤቶች ጉዳይና በከተማ ልማት ዲፓርትመንት በኩል (HUD)**
**የኪራይ እገዛ ለማግኘት ጥያቄ ካቀረቡ ወይም እያገኙ ከሆነ**
**ሊያውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮች**

## EIV ምንድን ነው?

EIV በHUD የኪራይ እገዛ ፕሮግራም የሚሳተፉትን ግለሰቦች የቅጥርና የገቢ መረጃ አካትቶ የያዘ ድረ-ገጽን መሠረት ያደረገ የኮምፒውተር የአሠራር ሥርዓት ነው። ይህ መረጃ HUD "ተገቢው ግለሰብ ተገቢውን ጥቅም ማግኘቱን" እንዲከታተል ያስችለዋል።

## በEIV ውስጥ የሚቀመጠው ምን ዓይነት የገቢ መረጃ ነው? ደግሞስ የሚገኘው ከየት ነው?

**የማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር፦**
የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች
የተጨማሪ ዋስትና ገቢ ጥቅማ ጥቅሞች
የድርብ ባለመብትነት ጥቅማ ጥቅሞች

**የጤናና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት የአዲስ ተቀጣሪዎች ብሔራዊ ማውጫ ፦**
ደሞዞች
የሥራ አጥነት ክፍያ
አዲስ ቅጥር (W-4)

## EIV ውስጥ የተቀመጠው መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው ለምን ዓላማ ነው?

የEIV ሲስተም እርስዎ የሚኖሩበት ቤት ባለቤት እና/ወይም ሥራ አስኪያጅ የገቢ መረጃዎንና የቅጥር ታሪክዎን የሚመለከት መረጃ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ይህ መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጣይ የሆነ የኪራይ እገዛ ለማግኘት ድጋሚ ማረጋገጫ በሚያገኙበት ጊዜ HUD የቅጥር እና/ወይም የገቢ ሁኔታዎን ገለልተኛ በሆነ መንገድ ማጣራትን በሚመለከት ያስቀመጠውን መመዘኛ ለማሟላት ይሆናል። ባለቤቱ ወይም ሥራ አስኪያጁ ይህንን መረጃ ለማግኘት የገቢ ምንጭዎን በቀጥታ ጠይቀው ከሚያጣሩ ከEIV ሲስተም ማግኘታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም በትንሽ ወጪ ብቻ ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ መረጃ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

የቤት ባለቤቶች እና ሥራ አስኪያጆች የEIVን ሲስተም መጠቀም የሚችሉት የሚከተሉትን ነገሮች ለማረጋገጥ ነው፦

- ገቢዎ በትክክል ሪፖርት መደረጉን

ከዚህም በተጨማሪ የሚከተሉትን ነገሮች ማጣራት ይችላሉ፦

የሐሰት የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር ተጠቅመው እንደሆነ
የትዳር ጓደኛዎን ወይም የሌላ የቤተሰቡን አባል ገቢ ሪፖርት ሳያደርጉ ቀርተው ወይም ቀንሰው ሪፖርት አድርገው እንደሆነ
በሌላ መኖሪያ ቤት የኪራይ እገዛ አግኝተው እንደሆነ

## እኔን የሚመለከት መረጃ ከEIV ለመውሰድ የእኔ ስምምነት ያስፈልጋል?

አዎን። መረጃ ይፋ እንዲደረግ ማሳወቂያና የስምምነት መግለጫ የተባለውን HUD-9887 ቅጽ እንዲሁም መረጃ ይፋ እንዲደረግ የተሰጠ የአመልካች/የተከራይ ስምምነት የተባለውን HUD-9887-A ቅጽ ሲፈርሙ HUD እና የንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የቅጥር እና/ወይም የገቢ ሁኔታዎን በማጣራት ለHUD የኪራይ እገዛ ብቁ ይሆኑ እንደሆነና እንዳልሆነ ለመወሰን ይችሉ ዘንድ እርስዎን የሚመለከት መረጃ እንዲሰጣቸው መስማማትዎ ነው። የስምምነት መግለጫ ቅጾቹን ሳይፈርሙ መቅረትዎ እገዛውን እንዳያገኙ ሊያደርግዎ ወይም ያገኙት የነበረው የመኖሪያ ቤቶች እገዛ እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል።

## የEIVን መረጃ ማየት የሚችለው ማን ነው?

እርስዎን የሚመለከተውን የEIV መረጃ ማግኘት የሚችሉት እርስዎና ሲፈርሙት በሚገባዎ HUD-9887 የስምምነት ቅጽ ላይ የተጠቀሱት ወገኖች ብቻ ናቸው።

## ያሉብኝ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

በHUD የሚታገዝ የመኖሪያ ቤት ተከራይ እንደመሆንዎ መጠን ለመኖሪያ ቤት እገዛ ባቀረቡት ማመልከቻና የሚያገኙትን እገዛ ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ በሚውለው (HUD-50059) ቅጽ ላይ የሰፈሩት መረጃዎች ትክክለኛና ሐቀኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። ይህ ጉዳይ በንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ በየዓመቱ ሊሰጥዎ በሚገባው በተከራዮች መብና ግዴታ ብሮሹር ላይም ተገልጿል።

**የተሳሳተ መረጃ መስጠት የሚያስከትለው ቅጣት**

የተሳሳተ መረጃ መስጠት ማጭበርበር ነው። የማጭበርበር ተግባር በሚፈጽሙ ላይ የሚጣሉት ቅጣቶች ከቤት ማስወጣት፣ አላግባብ ያገኙትን የእገዛ ክፍያ መልሰው እንዲከፍሉ ማድረግ፣ እስከ 10,000 ዶላር የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፣ እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስር፣ ወደፊት ምንም ዓይነት የኪራይ እገዛ እንዳያገኙ መከልከል እና/ወይም በግዛቱ ወይም በአካባቢው መስተዳድር የሚጣሉ ቅጣቶችን ሊያካትት ይችላል።

**ራስዎን ከችግር ይጠብቁ፣ የHUDን የሪፖርት አላላክ አሠራር ይከተሉ**

ማመልከቻዎችን ወይም የድጋሚ ማረጋገጫዎችን በሚሞሉበት ጊዜ የራስዎን ወይም የማንኛውንም የቤተሰብ አባልዎን የገቢ ምንጮች ማካተት ይኖርብዎታል። አንዳንዶቹ የገቢ ምንጮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

የደሞዝ ገቢ
የማኅበራዊ ደህንነት ክፍያዎች
የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች
የማኅበራዊ ዋስትና (SS) ወይም የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI) ጥቅማ ጥቅሞች
የተመላሽ ወታደሮች ጥቅማ ጥቅም
ጡረታ ወዘተ
ከቋሚ እሴቶች የሚገኝ ገቢ

ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

የሚከተሉትን የመሳሰሉ በልጅ ምክንያት የሚገኙ ክፍያዎች፦

- *የልጅ እገዛ*
- *የAFDC ክፍያዎች*
- *የልጆች ማኅበራዊ ዋስትና ወዘተ*

የሚያገኙት ገንዘብ እንደ ገቢ መቆጠር ይኖርበት እንደሆነና እንዳልሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ የንብረቱን ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁን ይጠይቁ።

በቤተሰብዎ ገቢ ወይም አወቃቀር ረገድ ለውጥ ከተከሰተ የኪራይ እገዛዎ ላይ ለውጥ ያመጣ እንደሆነና እንዳልሆነ ለማጣራት ወዲያውኑ ለንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ያሳውቁ።

የንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ "የሚከፍሉት ኪራይ መጠን የሚወሰነው እንዴት ነው?" የሚለውን የመረጃ ሰነድ ቅጂ ሊሰጥዎ ይገባል። ይህ ሰነድ በገቢዎ ውስጥ የሚካተተውና የማይካተተው ምን እንደሆነ የሚገልጽ ዝርዝር የያዘ ይሆናል።

## ከEIV መረጃ ጋር ካልተስማማሁስ?

EIV ላይ ባለው የቅጥር እና/ወይም የገቢ መረጃ የማይስማሙ ከሆነ ይህንኑ ጉዳይ ለንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ያሉበት መኖሪያ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ እርስዎ ያልተስማሙበትን የቅጥር እና/ወይም የገቢ መረጃ በተመለከተ ከገቢ ምንጩ ለማረጋገጥ በቀጥታ እነርሱን ያነጋግራል። ያሉበት መኖሪያ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ከገቢ ምንጩ መረጃውን እንዳገኘ ውጤቱን በጽሑፍ ያሳውቅዎታል።

## ከዚህ ቀደም ገቢዬን ሳላሳውቅ አሁን በEIV ሪፖርት ቢደረግስ?

የEIV ሪፖርት እርስዎ ሪፖርት ሳያደርጉ የቀሩትን ቀደም ሲል የነበረን ገቢ ሪፖርት የሚያደርግ ከሆነ ሁለት አማራጭ ይኖርዎታል፦ 1) ሪፖርቱ ትክክል ከሆነ የEIVን ሪፖርት መቀበል ወይም 2) ሪፖርቱ ትክክል አይደለም ብለው የሚያምኑ ከሆነ ሪፖርቱን ማስተባበል ይችላሉ። ከዚያም ያሉበት መኖሪያ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ የገቢ ምንጩን ሪፖርት ካደረገው አካል በጽሑፍ የሚቀርብ የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲሰጥ ያደርጋል። የገቢ ምንጩ ይህ ሪፖርት ትክክል መሆኑን ካረጋገጠ ያላግባብ ያገኙትን ትርፍ የኪራይ እገዛ ክፍያ ወደኋላ እስከ አምስት (5) ዓመት ድረስ መልሰው እንዲከፍሉ የሚደረግ ሲሆን ገቢዎን ሆን ብለው ለመደበቅ እንደሞከሩ ከተረጋገጠ መቀጮም ሊጣልብዎ ይችላል።

## EIV ላይ ያለው መረጃ እኔን የማይመለከት ቢሆንስ?

EIV የማንነት ስርቆት ሙከራዎችን ለማጋለጥ የሚያስችል አቅም አለው፤ ምናልባት የእርሰዎን የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር የተጠቀመ ሰው ይኖር ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ መኖሩ ከታወቀ በነጻ የስልክ መስመር 1-800-772-1213 በመደወል ለማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር ማሳወቅ ይኖርብዎታል። የማንነት ስርቆትን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው የማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ፦ http://www.ssa.gov/pubs/10064.html።

ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

## ገቢዬ ወይም የኪራይ እገዛዬ በትክክል ሳይሰላ ቢቀር የማነጋግረው ማንን ይሆናል?

በቅድሚያ ካሉበት መኖሪያ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ማብራሪያ ይጠይቁ።

ተጨማሪ እገዛ ካስፈለገዎ የሚኖሩበትን መኖሪያ የውል አስተዳዳሪ ማነጋገር ይችላሉ። ያም ሆኖ ጉዳዩ አጥጋቢ በሆነ መንገድ እልባት እንዳገኘ ሆኖ ካልተሰማዎ HUDን ማነጋገር ይችላሉ። የውል አስተዳዳሪውን አድራሻ የሚመለከት መረጃ ጭምር ሊሰጥዎ የሚችለውን በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የHUD ቢሮ በማግኘት ረገድ እገዛ ካስፈለገዎ በስልክ ቁጥር 1-800-685-8470 ለ ይደውሉ።

## EIVንና የገቢ ማረጋገጫ ሂደቱን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው ከየት ነው?

ያሉበት መኖረያ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ስለ EIVም ሆነ ስለ ገቢ ማረጋገጫ ሂደቱ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎ ይችላሉ። ከዚህም ሌላ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችሉ ዘንድ አግባብ ወዳለው የውል አስተዳዳሪ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የHUD ቢሮ ሊመሩዎ ይችላሉ።

ኮምፒውተር ማግኘት የሚችሉበት አጋጣሚ ካለ ደግሞ www.hud.gov/offices/hsg/mfh/rhiip/eiv/eivhome.cfm ከሚለው ድረ-ገጽ የHUD መነሻ ገጽ ላይ ስለ EIV እና ስለ ገቢ ማረጋገጫ ሂደቱ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።